# አገር እንዴት ሰነበተች ቁጥር 38

ጥቅምት 27 ቀን 2015ዓም(06-11-2022)

ባሳለፍነው ሳምንት በአገራችን የሰሜኑ ክፍል የሚካሄደው ጦርነት፣በወለጋና በሌሎቹ ክፍላተሃገር የንጹሃን መጨፍጨፍ፣መፈናቀልና የአዲስ አበባን የመዋጥ ሂደት ሳያባራ የቀጠለበት ሰሞን ነበር።በዚሁ ሳምንት ውስጥ በወያኔና በኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መካከል በደቡብ አፍሪካ ከተማ በፕሪቶሪያ ሲካሄድ የነበረው ድርድር ከመጨረሻው ጠርዝ ላይ ደርሶ በስምምነት ፊርማቸው ያረጋገጡበትን ይፋዊ መግለጫና ትዕይንት ያዬንበት ሰሞን ነው። ስምምነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም እንዲሰፍን የማድረግ ጥረት እንደሆነ ሁሉም ተደራዳሪና አደራዳሪ ሲያብራሩና ሕዝቡም በጉጉት ይጠብቀው የነበረ መሆኑ የሚካድ አይደለም።

ኢትዮጵያ ሰላም አጥታ ላለፉት 50 ዓመታት ስትታመስ መኖሯ፣ሕዝቧም እንዲሁ የሰላም አዬር ሳይተነፍስና የስጋት ኑሮ ሲኖር ቆይቷል።ከዚህ አስከፊ ኑሮ ለመውጣት የሚያስችል እውነተኛ ሰላም ቢሰፍን የሁሉም ፍላጎት ስለሆነ የሚቃወምና የሚጠላ የለም።ጥያቄው በድርድሩ የተደረሰበት የስምምነት ውሳኔ እውነት ኢትዮጵያን ካለችበት ቀውስና የመበታተን አደጋ በዘለቄታው ያድናታል ወይ? ሕዝቡስ የሚጠይቀውንና እዬታገለ ብዙ መስዋእትነት የከፈለለት ሰላሙ ተጠብቆለትና ተረጋግጦለት፣የአገሪቱ ባለቤት መሆኑ ታምኖበት፣ዜግነቱ ተከብሮለት፣ በፈለገበት ቦታ ሄዶ የመኖርና የመሥራት፣ሃብት የማፍራት መብቱ ይረጋገጥለታል ወይ?የሚለው ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው።

ባለፈው ስርጭታችን ለማሳዬት እንደሞከርነው የሰሞኑንም የድርድር ሂደት እስከነውጤቱ ባደረግነው ጥናትና ክትትል እንደደረስንበትና እንደተረዳነው ከሆነ ፣ላለፉትም ዓመታት ስናንጸባርቀው የቆዬነውን አቋማችንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በሁለቱ ጸረ ኢትዮጵያ በሆኑት ቡድኖች ፣በኢሕአዴ ልጆች መካከል በህወሃትና በኦነግ ኦህዴድ ብልጽግና መካከል የተፈጸመው ድርድርና የደረሱበት ስምምነት ለአገራችንና ለሕዝቧ ዘላቂ ሰላም ያመጣለታል ብለን አናምንም።ደግመን ደጋግመን እንዳሳዬነው ፣ ሌላውም እንደሚያምነው ግጭቱ የተነሳውና ከግማሽ ሚሊዮን በላይ የሚሆን ዜጋ የረገፈበት ጦርነት የተቀሰቀሰው በሥልጣን ሽኩቻና በጥቅም ድርሻ እንደሆነ ማንም አይዘነጋውም።ይህም ማለት ጦርነቱ የኢትዮጵያን አንድነት በሚቀናቀንና በማይንቀናቀን፣በተገንጣይና አንድነትን በሚያስከብር ሃይል መካከል አይደለም ማለት ነው።ሁለቱም የአገርን አንድነት የሚጻረር በሕገ መንግሥት በሚሉት ሽፋን የተሰናዳ ሕገ ጥፋት መመሪያ ተቀብለው በተግባር ለመተርጎም በአንድ እረድፍ የተሰለፉ ቡድኖች ናቸው።

ደግመን ደጋግመን እንደገለጽነው የሁለቱም ጥቅም ከተከበረላቸው በድርድር የማይስማሙበት መንገድ እንደማይኖር በግልጽና በድፍረት ለማሳዬት ሞክረናል።ወያኔ የክልሉ ዋና ባለቤት ሆኖ በመንበሩ ላይ መልሶ እንዲቀመጥ ፣ሕገ ጥፋቱ ሳይሸራረፍ ተከብሮ ለማንኛውም ጥያቄ የወልቃይትና ጠገሌ፣የራያና አዘቦ የይገባኛል ጥያቄ ጭምር በዚያው መመሪያና ደንብ መሠረት መልስ የሚሰጠው በመሆኑ፣የአንቀጽ 39 የመገንጠል መብት ተከብሮ ሁሉንም ያካተተ ብሔራዊ ጉባኤ በሚለው ሽፋን ኢሕአዴግ የፈለፈላቸው በዬአካባቢው የሚንቀሳቀሱና ሰላም የሚነሱ ተስፈንጣሪ ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑ ቡድኖች እውቅና አግኝተው የመገነጣጠል መብታቸው የሚረጋገጥበት የኮንፌዴሬሽን አወቃቀር እንዲሰፍን ፣ ከዚያም አልፎ ተርፎ በአገሪቱና በሕዝቡ ላይ ወንጀል የፈጸሙ በሕግ የማይጠዬቁ መሆናቸው

ስለተረጋገጠ ለመስማማት ችለዋል።እነዚህን የሚያጸድቅ ውል ባይሆን ኖሮ ላለመስማማት ይችሉ ነበር። ለፊርማ እጃቸውን ዘርግተው ለመፈራረምና ለመጨባበጥ ባልበቁም ነበር።

በኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግናም በኩል እንዲሁ መንግሥትነቱ ካልታወቀለት፣የጀመረውን አገር እያፈረሰ የኦሮሚያ አገራዊ ምሥረታ እንዲቀጥልበት ፋታና ዕድል ካላገኘ ለመፈራረም እጁን አያሾልም ነበር።ይህ ማለት በድርድር በኢትዮጵያና በኢትዮጵያውያን ኪሳራ ላይ ቁማር ተጫውተው በእኩል ደረጃ የሚሹትን አግኝተው የተለያዩበት ድርድር ነበር ማለት ነው።በጣም የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር ይህንን ሴራ ለመገንዘብ ያልቻለው ሰላም ሰፈነ እያለ ጉሮ ወሸባዬ ማለቱ ነው።የእምነት አባቶች፣ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች(ለሥልጣን የሚፎካከሩ እንጂ ዓላማ ሰንቀው የመንግሥትን ሴራና ስርዓት ተገንዝበው የሚቃወሙና ለተሻለሥርዓት መስፈን የሚታገሉ ባለመሆናቸው ተቃዋሚ ድርጅቶች ብለን አንጠራቸውም)፣ምሑራን ተብዬዎች፣አድር ባይ ጋዜጠኞችና የጥቅም ተካፋዮች፣የውስጥም የውጭም የኢትዮጵያ ጠላቶች ስምምነቱን እንደ ትልቅ እምርታና ቁም ነገር ቆጥረው ሲደግፉ ለማዬት ችለናል።

በዚህ ድርድር የምንሻው ሰላም አይገኝም፣የኢትዮጵያ አንድነትም አይረጋገጥም።በዚህ ድርድር የኢሕአዴግ ቤተሰቦች የፈጠሩትን የሥልጣን ሽኩቻ አሶግደው አንደ ቀድሟቸው ተባብረው የቆሙለትን አገር ያመበታተን አቅጣጫ ለማስቀጠል የተስማሙበት እንጂ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለተሻለ ሥርዓትና ሰላም የሚያበቃ አይደለም።በነሱም ሊመጣ አይችልም።በሰሜኑ ያገሪቱ ክፍል በተለይም በትግራይ መሬት ጦርነቱ ቆመ ማለት በአገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄደው ያሸባሪዎች ጭፍጨፋ፣ መፈናቀልና የንብረት ዘረፋና ውድመት ቆሟል ማለት አይደለም።ይህ እስካልቆመ። ድረስ ሰላም የለም፣ አይኖርምም።በሁለቱ አገር አጥፊ ቡድኖች መካከል የተደረሰው ስምምነት በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነት ላይ የተገኘ ድል ነው።ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ከዚህ ያተረፉት ቤሳ ቢስትኒ የለም። የድሉ ባለቤቶችም አይደሉም።

አብይ አህመድ ኢትዮጵያዊነትን የመደበቂያ ዋሻ አድርጎ ሕዝቡን እዬዋሸ መሄዱን እንኳንስ እኛ ኢትዮጵያውያን ሌላውም የውጭ አገር ዜጋ የሚያውቀው ጉዳይ ነው።በቅርቡ የኒውዮርክ ጋዜጠኛ ያወጣውን ሰነድ ማስታወሱ በቂ ነው።አብይ አህመድ በሰሞኑ ባደረገው ንግግሩ ኢትዮጵያ ለሰላም ስትል የማትሰጠው አይኖርም ማለቱን በጆሯችን ሰምተናል።ይህ ማለት ወያኔ ኢትዮጵያዊ ስለሆነ ለሱ የሰጠውን ዕድል ማለቱ ሳይሆን ለሱዳን 50Xበ1600 ኪሎሜትር ስፋት ያለውን ለም የእርሻ መሬት አሳልፎ መስጠቱን፣ለግብጽም የግድቡን ሥራ በሚፈልጉት መንገድ እንዲካሄድ ማድረጉን የሚያሳይ ነው።ሌሎችም የጎረቤት አገራት የድንበር ላይ መሬት ጥያቄ ወይም ሌላ የጥቅም ጥያቄ ቢኖራቸው አሳልፎ ለመስጠት ዓይኑን እንደማያሽ ያረጋገጠበት ንግግሩ ነው።ለምዕራባውያንም ከቃላት ባለፈ የሚፈልጉትን ያገሪቱን ንብረትና ተቋማት በማዘመን ስም እዬቸበቸበ አሳልፎ ሰጥቧቸዋል፤የቀሩትንም ለመስጠት ዝግጅቱን ቀጥሎበታል።ለገንዘብ ሲል ያገራችንን ልዑላዊነት በማስደፈር ላይ ነው። ምዕራባውያኑ እንደ ወያኔ ሕገመንግሥቱ ይከበር ሲሉም አገሪቱ ትበታተን ማለታቸው እንደሆነ የታወቀ ነው።ኢትዮጵያን እርቃኗን ካስቀሩ በኋላ ተበታትና በቀላሉ የሚቆጣጠሯቸው ጥቃቅን መንደራዊ አገዛዞች ቢኖሩ ይመርጣሉ።ለሌሎቹም ያፍሪካ አገሮች የመበታተን መነሻና ቤተ ሙከራ የሚያደርጉት አገራችንን መሆኑን መረዳት አለብን።አሜሪካኖች ለኢትዮጵያውያን የ18 ወራት ጊዜያዊ መኖሪያ ፈቃድ መስጠታቸውም ያገራችንን የወደፊት አስከፊ ጉዞ ከማጤን የመጣ እንጂ ከደግነት በመነሳት አይደለም። ደግማ ቢሆኑ ኖሮ ልጅና ወላጆችን እንዳይገናኙ ለማድረግ በሜክሲኮ ድንበር ላይ በገነቡት እረጅም አጥር ሥር ለወራት ፈሰው ብርድና ሙቀት የሚፈራረቅባቸውን የጎረቤቶቻቸውን አገር ሕዝብ ባላሰቃዩት ነበር።

ምዕራባውያኑ ለሰላም ንግግሩ በወያኔ ጀርባ ሽንጣቸውን ገትረው የቆሙት ኤርትራንም በመዳፋቸው ውስጥ አስገብተው ለመቆጣጠርና በከባቢው የቻይናና የሩስያን እንቅስቃሴና ተሳትፎ ለማገታት ሲሆን ያንን በተላላኪነት የሚያስፈጽምላቸው ወያኔ ነው ብለው ስለሚያምኑ ተመልሶ ከቦታው ላይ እንዲቀመጥላቸው በመሻት ነበር፤ስምምነቱም ያንን ያረጋግጥላቸዋል። ያ ባይሆን ኖሮ ለመፈራረም የሚደርሱበት ዕድሉ የመነመነ ነበር።የአደራዳሪው ቡድን ለስሙ የአፍሪካ ህብረት ተባለ እንጂ ዋና አሸከርካሪና ወሳኞቹ ምዕራባውያን በተለይም አሜሪካኖቹ ናቸው።ለዚያም ነው በኢትዮጵያ ኪሳራ ላይ የተደረገ ስምምነት ነው ያልነው።

የድርድሩ ውሳኔ በብዙ ገጽ ላይ የሰፈረ ሲሆን 12 ዋና ዋና እርእሶችን ያካተተ ነው።ከነዚያ ውስጥ ዋናዋናዎቹ ስናወጣ የሚከተሉትን ይመስላሉ።

1 የሕገ መንግሥቱ መከበር

2 በአንድ አገር ውስጥ አንድ መከላከያ ብቻ መኖሩንና የትግራይ መከላከያ ሠራዊት የሚለው ቀርቶ በሌሎቹ ውስጥ ማለትም በመከላከያ፣በልዩሃይልና በሚሊሽያ ውስጥ እንዲካተት

3 በሕገመንግሥቱ መሰረት ሁሉም ጉዳይ መታዬትና መፈታት እንዳለበት

4 ሁሉንም ያካተተ ጉባኤ እንዲካሄድ

5 የትግራይ ክልላዊ መንግሥት እንደሌላው ክልላዊ መንግሥት ሆኖ በብልጽግና ስር እንዲንቀሳቀስ

6 ምርጫ ተካሂዶ ተወካዮቹን በፌዴራሉ የሕዝብ ምክርቤትና በሌሎቹ ተቋማት ውስጥ የሥራ ድርሻ እዲኖረው

7 የጥላቻና የውንጀላ ፍረጃዎች እንዲወገዱና በወንድማማችነት መተያዬት እንዲኖር

8 ከብልጽግና መንግሥት በስተቀር ሌላው ከውጭ አገራት መንግሥታት ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ

9 የሰብአዊ አገልግሎቶችና እርዳታዎች ካለምንም ገደብ እንዲዳረሱ፣የተቋረጡት በአስቸኳይ እንዲቀጥሉ

ከላይ በመግቢያችን ላይ እንዳቀረብነው ለጦርነቱ መነሻ የሆኑት እነዚህ የውሳኔ ነጥቦች ነበሩ። በጊዜው የአብይ አህመድ መንግሥትና የወያኔ መሪዎች ለሰላም የተነሱ ቢሆን ኖሮ የውጭ ሃይል ሳይገባ ችግሩ በአገር ውስጥና በአገር ሽማግሌዎች መፈታት በተቻለ ነበር።የብዙ መቶ ሽህ ንጹሃን ደም በከንቱ ባልፈሰሰም ነበር።ግን ነገሩ ሌላ ነበርና ፣ግለኝነትና እልህ ተጨምሮበት ሁለት ዓመት የዘለቀ ጦርነትና እልቂት፣የብዙ ሃብት ውድመት ሊያስከትል ችሏል።አሁንም ቢሆን የሁለቱ ስምምነት ላይ መድረስ ዘላቂ ሰላም በአገራችን ላይ ሰፈነ ማለት አይደለም።እንደቀድሟቸው ተባብረው የቆሙለትን አገር የማፍረስ ሥራ እንዲቀጥሉበት ፋታ የሚሰጥ ከመሆን አያልፍም።

ሕገ መንግሥት የሚሉት የጥፋት ሰነድ ሁለቱንም የሚያስተሳስራቸው የጋራ ቃል ኪዳን ነው።በዚህ የቃል ኪዳናቸው ሰነድ ውስጥ አንቀጽ 39ኙን የመሰለው ኢትዮጵያን የመበታተን ሴራ ቁልጭ ብሎ ተቀምጧል።የትኛውም ክልል በቃኝ፣አብሬ አልኖርም፣የራሴን አገር እመሰርታለሁ ካለ ከፌዴራሉ ሊነጠልና የብቻውን ከባቢ ይዞ አገር ሊሆን ወይም ከሌላው አጎራባች አገር ጋር ሊቀላቀል ይችላል።

በዚህ ሕገመንግሥት ስም አንዱ ክልል የሌላውን ክልል መሬት በሃይሉ ሊወስድና ሊወስንበት ይችላል ማለት ነው።ወያኔ የወልቃይትና ጠገሌን፣የራያና አዘቦን መሬት ለ27 ዓመት በሃይል ወሮ መያዙ

ሲታወቅ በሕገመንግሥቱ መሰረት ይወሰንበት ማለቱ በሥልጣን ላይ በቆዬበት ጊዜ ያሰፈረው የትግራይ ተወላጅ ቁጥሩ ከፍተኛ በመሆኑና ከሶስት ዓመት ወዲህ በመመናመኑ አሁን ተመልሶ ይሰፈርና ድምጽ ይስጥበት በማለቱ ቦታውን መልሼ እይዛለሁ በሚል ተስፋ ተነስቶ ሲሆን ከብልጽግና አጋሩ ጋር የደረሰበትም ስምምነት ያንኑ እውቅና የሚሰጥ ነው።በመሃሉ የሚጎዳውና መጫወቻ የሆነው የቦታዎቹ ባለቤት ሆኖ ለዘመናት የኖረው በብዛት የአማራው ማህበረሰብ ነው። ምዕራባውያን እነዚህን ቦታዎች ምዕራብ ትግራይ በማለት የሚጠሩትም ለዚህ መዳረሻ ነው።ከሕዝበ ውሳኔው በፊት እውቅና መስጠታቸው ነው።

"የማይተማመን ባልንጀራ በዬወንዙ ይማማላል"እንደሚባለው በአፈጻጸሙ ላይ የማይስማሙበትና ለዳግም ጦርነት የማይነሱበት ምክንያት አይኖርም።ሌባ ሲሰርቅ ይስማማል ሲካፈል ይጣላል እንደሚባለው በሥልጣንና በጥቅም ክፍፍሉ ላይ ጠባቸው ማገርሸቱ አይቀርም።

ወያኔን በወታደራዊ ሃይል በልጦ ጦርነቱን በአሸናፊነት ለመቋጨት ያላስፈለገበት ዋናው ምክንያት የዓላማ አጋር በመሆናቸው የጀመሩት የጋራ ሥራ ስላልተጠናቀቀና፣የሁለቱም የጋራ ጠላት የሆነው ኢትዮጵያዊነትና በተለይም የአማራው ማህበረሰብ እዬተደራጀ በመምጣቱ ባደረባቸው ስጋት የተነሳ ነው።ይህንን የተከሰተበትን አደጋ ለማስገድ አማራውን በተለያዩ መንገዶች ማዳከሙ እንደዋና ምርጫና ስልት ተደርጎ ተወስዷል።የራያና አዘቦን፣የወልቃይትና ጠገሌን ኑዋሪ ሕዝብ ላለፉት ሁለት ዓመታት ማግኘት የሚገባውን የባጀት ሙብት በመንፈግ የትግራይ ክልል አካል በሚል ስበብ ለድህነት ማጋለጡ በችግር እጁን ይሰጣል ከሚል ጨካኝ አስተሳሰብ የሚነሳ አቋም ነው።ሕዝበ ውሳኔ የሚሉት የማወናበጃ ትርክት ሳይስተገበር ቀድሞ ውሳኔ የሰጡበት መሆኑን ያሳያል።ይህ ግን በአካባቢው ሰላም ያሰፍናል ማለት ሳይሆን ለተራዘመና እጅግ ለከፋ እልቂት የሚዳርግ ውሳኔ ነው።የትግራይና የአማራው ማህበረሰብ ሲጫረስ ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና የቤት ሥራውን ይሠራል፤በታሪክ ያልተበረች ኦሮሚያ የተባለች አገር ለመፍጠር የሚችልበትን ሌላውን እዬዘረፈ የአቅም ግንባታ ያካሂዳል።ይህንንም በስንዴ ምርት ሰበብ አሳይተውናል።ኦሮሚያ እንደ ኡክሬን ስንዴ እያመረተች ሌላው ምንም አይነት የልማት እንቅስቃሴ ሳይኖረው የሷን እጅ ጠብቆ፣ ጥገኛ ሆኖ ሊያድር እንደሚችል በግልጽ አሳይተውናል።ወያኔ ሌላው እዬደማ ትግራይ ብቻ ትልማ ይል የነበረውን መመሪያ አሁን ኦነግ ኦሕዴድ በተራው ሌላው እዬደማ ኦሮሚያ ትልማ በሚለው መለወጡን የማያጤን ካለ እውነትም ጅልና ጅላጅል ነው።

በጦርነቱና በኤኮኖሚው የበላይነቱን ከአንድም ሁለት ሶስቴ ያገኘው የብልጽግና ስብስብ ገፍቶ ያልሄደው ወደፊት ይነሳብኛል ብሎ የሚፈራው የኢትዮጵያውያን በተለይም የአማራውን መቅሰፍት ከወያኔ ጋር በጋራ ልከላከል እችላለሁ፤እንዳለፉት ሶስት ጊዜዎች በቅርበት እየተዋጋ ይመክትልኛል፣ እንዳያንሰራራ ያደርግልኛል ብሎ እንጂ ሥልጣኑን ተካፍሎ የማደር ፍላጎት ኖሮት አይደለም። ኦነግ ለሁለቱም ማለትም ለትግራይና ለአማራው ማህበረሰቦች ብቻም ሳይሆን በኢትዮጵያዊነታቸው ለሚያምኑት ለሌሎቹ ማህበረሰቦች፣ለኦሮሞ ተወላጆች ጭምር የሚራራ አንጀት የለውም። የኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና እንኳንስ የኢትዮጵያን መሬት ሁሉም ኬኛ በሚለው የስግብግብ ሩጫ የጎረቤት አገራትንም በኦሮሙማ ልክፍት ለመበከልና ለመጠቅለል ዕቅድ ዘርግቷል።

በአጠቃላይ ወያኔና ኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና ደረሱበት የተባለው ስምምነት ኢትዮጵያን ለዘላቂ ሰላም የማያበቃት ሳይሆን የሁለት ሌቦች ስምምነት ከመሆን ያለፈ ነው አንልም።ይህንን እውነታ ለመሸፋፈን ተከፋይ ጋዜጠኞችና ውታፍ ነቃዮች ላንቃቸው እስኪሰነጠቅ፣ቀለማቸው እስኪደርቅ ድረስ በመንጫጫትና በመጫጫር ላይ ናቸው።እውነቱን ግን የሚለውጠው የለም፤ጉድና ጅራት ከኋላ ነውና እያደር እናዬዋለን።አሁንም ደግመን ደጋግመን የምንለው ቢኖር የጎሰኞቹ ሥርዓትና የሚመሩበት ሕገ ጥፋት እስከወዲያኛው ድረስ ካልተወገደ በአገራችን ሰላም አይሰፍንም።ኢትዮጵያ በኢትዮጵያውያን

አገር ወዳዶች ካልተመራች ህልውናዋና ልዑላዊነቷ ለአደጋ የተጋለጠ ነው።አብይ አህመድ ወያኔ ሲወድቅ የፈጠራቸው እንደ ሸኔ ያሉት ሁሉ አብረው ይወድቃሉ ሲል ተናግሮ ነበር።አሁን ወያኔ አልወደቀም፣አልተወገደም፤ስለሆነም የፈጠራቸው ጉጀሌዎች ሁሉ አብረውት ይዘልቃሉ ማለት ነው። ለዚያም ነው እነሱም የተካተቱበት ጉባኤ ይካሄድ በማለት ወያኔ አጥብቆ የተከራከረውና የስምምነቱ አካል ሆኖ ተቀባይነት እንዲኖረው ያደረገው።

አገራችን የውሸት ወፍጮና ፋብሪካ የተተከለባት አገር ሆናለች።የተተከለው የውሸት ወፍጮና ፋብሪካ ካልተነቀለ ሰላምና እውነት አይኖርም።የውሸት ወፍጮ መጁን የጨበጠው አብይ አህመድና የውሸት ፋብሪካ የሆነው ኦነግ ኢሕዴድ ብልጽግና ስብስብና አጃቢዎቹ የኢትዮጵያውያንን ሃይማኖታዊ እሴት፣ መልካም ባህልና ስነምግባር በክለውታል።በጭካኔና በእራስ ወዳድነት ለውጠውታል።ነብዩ ሞሃመድ ሳይቀር የእውነተኛና የፍትህ አገር ብሎ የመሰከረላት ኢትዮጵያ አሁን በመሪዋ በአብይ አህመድ ዘመን የውሸታም፣የጨካኞችና የክፉዎች አገር ተብላ ተሰይማለች። ድህነት ላልታደሉት አገሮች የጋራ ጸጋ በመሆኑ ልዩ ባያደርገንም በነዚህ እኩይ ተግባሮች ግን የተለዩን ፍጡሮች ሆነናል።ሕዝብ መሪውን፣ መሪውም ሕዝቡን ይመስላል የሚባለው አባባል በገሃድ የታዬባት አገር ብትኖር ኢትዮጵያችን ነች። ጥቂት ሃቀኞች የሉም ለማለት ሳይሆን ብዙሃኑ መበከላቸውን ባለመካድ ነው።

አብይ አህመድ ያልዋሸው የለም።የኢትዮጵያን ሕዝብ ዋሽቷል፤እዬዋሸም ነው።ከዷል እዬካደም ነው። የተባበሩት መንግሥታትን ዋና ጸሃፊ ጉተሬዝን ዋሽቷል፤ዋሽቶኛልም ብሏል።የሱዳኑን አልብሩሃንን ዋሽቷል፣የግብጹን አል ስሲንም ዋሽቷል፣የአውሮፓ ህብረትን ዋሽቷል፤የአፍሪካ መሪዎችን ቢዋሽም በነሱም ዘንድ ያለ ጸባይ ስለሆነ ገኖ አልታዬበትም እንጂ ዋሽቷቸዋል።ኢሳያስ አፈወርቂን ዋሽቷል፤ ወደፊትም ከመዋሸት ባለፈ ይፈነግለዋል።ለአብይ አህመድ ውሸትና ክህደት ጥበብና እውቀት ነው። የሱንም ብልሹ ምግባር ተቀብለው የሚያስተጋቡ፣ውሸታም ጋዜጠኞች፣መምህራን፣ተማሪዎች፣የእምነት አባቶች፣የፖለቲካ ድርጅቶችና አባላት፣ነጋዴዎች፣የኪነት ሰዎች እረ ምን ቅጡ መቀደዱን ሙያና የታማኝነት መግለጫ የጥቅምና የሥልጣን እጅ መንሻ አድርገውታል።ሕዝቡም እነሱ የዬፈጩ የሚጭኑበትን የውሸት ጆንያ ተሸክሞ ተምታቶበት ሲወላገድ ይታያል። በአገራችን የውሸት ወፍጮና ፋብሪካ ተተክሏል ያልነውም ለዚሁ ነው።ወፍጮው መነቀል አለበት!

ውሸትና ክህደት በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተናቀና የተጠላ ምግባር ነበር።በዘፈንና በእንጉርጉሮ ሳይቀር እውነትንና ሃቀኝነትን፣ታማኝነትን ሲያወድሰው ኖሯል።ከነዚያም መካከል የሚከተሉት አባባሎች ይመሰክራሉ።የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ፣በማለት የተናገሩት ወይም የገቡት ቃል ኪዳን ከወለዱት ልጅ ህይወት በላይ መሆኑን ያሳዩበት አባባል ነው።በመተማመን ላይም የሚከተለውን ይላሉ።

ፊርማና ወረቀት ጠፊ ነው ተቀዳጅ፣

መተማመን ብቻ ይበቃል ለወዳጅ።

ያምባሰል ማር ቆራጭ ይወጣል በገመድ ፣

አደራ ሲሰጡት ይጠብቃል ዘመድ።

ቃሉን ሳያከብር ለቀረና ለከዳቸው ደግሞ በሃዘኔታ

እንጠጣ ነበር ውሃ ባንድ ኩዳ ፣

በጣም ያሳዝናል ያመኑት ሲከዳ።

ሲወዱት የጠላ ሲያምኑት የከዳ ሰው፣

ከጅን ከጇ ይከዳው ብድሩ ይድረሰው።

በዚህ አይነቱ ስነምግባርና ባህል ታንጾ የኖረ ማህበረሰብ የኖረባት አገራችን ኢትዮጵያ አሁን ላይ የሌባ፣ ያድር ባይ፣የከሃዲ፣ያጭበርባሪ መኖሪያ ዋሻ ስትሆን ማዬቱ በጣም ያሳዝናል።ያ ደግሞ መንግሥታዊ መዋቅር ዘርግቶ መሪዎቹ የተካኑበትና የተጠመቁበት ጠበል ሲሆን ያሳፍራል።ሌላው ቀርቶ የሃይማኖት መሪዎችም ቢሆኑ ሰላም ወረደ ከሚለው ጫጫታ ወጥተው በዬ እስር ቤቱ የሚማቅቁት የሕዝብ ልጆች ይፈቱ ብለው ለመጠዬቅ እንኳን አልደፈሩም።እነሱም በውሸት ጠበል ተረጭተው የሚረጩ ሆነዋል። ተመስገን ደሳለኝ፣ታዲዎስ ታንቱና ሌሎቹም የፍርድ ውሳኔ ሳያገኙ በየጊዜው ዳኛ የለም፣እዬተባሉ ሲንከራተቱ ማዬትን የመሰለ ወንጀል የለም።ዳኛ ከሌለ ዳኝነት የለም ማለት ነው፤ዳኝነትም ከሌለ ፍትሕ የለም ማለት ነው።ታዲያ ፍትህ በሌለበት አገር እንዴት ሰላም ይወርዳል? በውሸት ትረካ የተያዘ መሬት በይጥናልህ በሚወሰንበት አገዛዝ ምን አይነት ፍትሃዊ ሥርዓት ይጠበቃል?ሰላም ሰፈነ ብለው ጮቤ የሚረግጡት መልስ ይስጡበት።

በመሬት ላይ ያለው ሁኔታ እንደሚያሳዬው ከሆነ በስምምነቱ ላይ ያልተደሰቱ የተዋጊ ጦሩ አባላትና የትግራይ ተወላጆች ጉም ጉም እያሉ መሆናቸው ይሰማል።ሕዝቡ ለዚህ ነወይ ልጆቻችንን የገበርነው? ለምን ከመጀመሪያው ላይ አልታረቃችሁም ሲል ተዋጊዎቹ ደግሞ ነጻ አገር ይኖራችኋል ብላችሁ ለእናንተ ሥልጣን መጠቀሚያ አደረጋችሁን ባዬች ናቸው።በፌዴራል መከላከያው አባላት በኩልም ከአንድም ሦስት ጊዜ ለማሸነፍና ለመደምሰስ ስንቃረብ እንድናቆም ተደርጎ ብዙ ወንድሞቻችንንና እህቶቻችንን ለማጣት ችለናል።የአሁኑስ እርቅ ለቀጣይ ጦርነት የማንሰለፍበት ምን ዋስትና አለ? በአጠቃላይ በሰራዊቱ ላይ ወንጀል የፈጸሙት በሕግ ሳይጠዬቁና የተበደሉት ሳይካሱ ምን አይነት ሰላም ይሰፍናል? የሚሉ ናቸው።ሁሉም የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ተገኘ ለተባለው ሰላም መደፍረስ ምልክቶች ናቸው።ወደኋላ መለስ ብለን ታሪክን ብናይ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት በአልጀሪያው የስምምነት ሂደት ስዩም መስፍን መዞ ባወጣው ውሸት ሕዝቡ እንደተታለለ የሚዘነጋ አይደለም። የአሁኑም የውሸት ጋጋታ ከዚያ የተለዬ አይሆንም።ዕድሜ ከሰጠን እናዬዋለን!

ክርስቶስ ከሁለት ሽህ ዓመታት በፊት ስለእውነት ሲያስተምርና ህይወቱንም የሰጠበት ትምህርቱ እስከ አሁን ድረስ የብዙሃኑን ልብ ሊገዛና ከሃጢአት ሊያርቃቸው አልቻለም።በተለይም የክርስቶስ ተከታዮችና መልእክተኞች ነን በሚሉት ይብሳል።ለእኛ እውነትን የተከተለ የዘላለም ህይወት ያገኛል ሲባል ከሞተ በኋላ ሳይሆን በምድር ላይ በሕይወት እያለ ከመከራ፣ከስቃይ፣ከጭንቀት፣ከእርስ በርስ ጥላቻና ግጭት፣ከጦርነት፣ከድህነት ነጻ በሆነች ምድራዊ ዓለም ይኖራል ማለት ነው።ለዚያ ደግሞ እውነትን የተከተለ ዓላማና ግብ የያዘ ትግል ማድረግ ተገቢ ነው፤ ዘለዓለማዊ ምድራዊ ሰላም በምኞትና በጸሎት የሚገኝ አይደለም እንላለን። ክርስቶስም በምድራዊ ህይወቱ ለግፉአን የቆመውና ያስተማረው፣ህይወቱንም አሳልፎ የሰጠው ለዚሁ አይነቱ እውነት ነበር ብለን እናምናለን።የሱ ተከታዮች ነን የሚሉት ግን ሕዝቡን በምድር ላይ የሚደርስብህን ስቃይና መከራ ቻለው፣ለመሪዎችህ ተገዛ፣እነሱ የፈጣሪ ምርጦችና ወኪሎች ናቸው በማለት እንዳይታገልና መብቱን እንዳይጠይቅ፣ እኩልነቱን እንዳያስከብር እንቅፋት ሆነውበታል።ፈጣሪ ከነዚህ አስመሳዬች ይልቅ ለፈጠረው የሰው ልጆች ጥቅምና ሰብአዊ ክብር ሲሉ ህይወታቸውን የሚሰጡትን ይመርጣል።እውነትን መናገር የክርስቶስን መንገድ መከተል ነውና በወያኔና በአነግ ኦሕዴድ ብልጽግና መካከል በተደረገው ስምምነት ዘላቂ ሰላም አይመጣም እንላለን።ጭራሽ ወደለዬለት መጠፋፋት፣ካለፈው ወደከፉ እልቂትና መከራ ውስጥ

የሚገቡበት ይሆናል።ያንንም ተከትሎ የውጭ ሃይሎች በቀጥታ ገብተው ያሻቸውን የሚያደርጉበት ዕድሉ ከፍተኛ ነው።ይህንን ከግምት ውስጥ አስገብቶ በጫጫታው ሳይወናበድ፣ ወይም በሴራው ሳይጠለፍና እጁን ሳይሰጥ አገር ወዳዱ  ከምንጊዜውም  በበለጠ መልኩ ተደራጅቶና ተሰባስቦ ለመፋለም ዝግጅት ማድረጉ ለነገ የማይባል ተግባር  ነው።

ለእውነተኛ ሰላም የእውነተኛ አገር ወዳዶች ህብረትና ትግል ወሳኝ ነው!

በወያኔና በኦነግ ኦሕዴድ ብልጽግና  በኩል ዘላቂ ጦርነትና መከራ እንጂ ዘላቂ ሰላም አይሰፍንም!!